Advocates for Youth
Rights. Respect. Responsibility.®

ሀቆቲ

እድገት እና መዳበር፣ 13-17 ዓመት እና ከዚያ በላይ ላለ እድሜ— ወላጆች ሊያውቁ የሚገባቸው።

የሰው ልጅ መዳበር፣ አካላዊ፣ ባህሪያዊ፣ ግንዝቤያዊ (cognitive)፣ ስሜታዊ የሆነ እድሜ ልክ የሚዘልቅ ሂደት ነው። በለጋ የልጅነት ዘመን -ከሕጻንነት እስከ ልጅነት፣ ከልጅነት እስከ ጉልምስና፣ ከጉልምስና እስከ አቅመ አዳም — በርካታ ለውጦች ይካሄዳሉ። በጠቅላላው በሂደቱ በሙሉ የእያንዳንዱን ሰው ምርጫዎችን የሚመሩ፣ ግንኙነቶችና ግንዛቤዎችን የሚወስኑ ባህሪያትንና እሴቶችን ያዳብራል።

ቋንጂናዊ መስህባዊነት (Sexuality) የሕይወት ዘላቂ ሂደት ነው። ጨቅላ ሕጻናት፣ ልጆች፣ ታዳጊዎች (teens) እና ጎልማሶች ጾታዊ (sexual) ፍጡሮች ናቸው። ልክ የወጣት ልጅ አካላዊ፣ ስሜታዊ እና ግንዛቤያዊ (cognitive) እድገቱን ማዳበር ጠቃሚ የመሆኑን ያህል፣ ለመስህባዊነት መዳበር አስፈላጊዊን መሠረት መጣል በጣም ጠቃሚ ነው። ዐዋቂዎች፣ እየዳበረ የሚጓዘውን መስህባዊነታቸውን፣ ወጣቶች፣ እንዲረዱትና እንዲቀበሉት የማድ ረግ ኃላፊነት አለባቸው።

እያንዳንዱ የእድገት ደረጃ የተወሰኑ ጉልህ አሻራዎች አሉት። የሚከተሉት የእድገት መዳበር መመሪያዎች፣ በዚህ የእድሜ ክልል ለሚገኙ ወጣቶች የሚ ውሉ ናቸው። ሆኖም እያንዳንዱ ወጣት ሰው ግለሰብ ሲሆን፣ ከሌሎች በተመሳሳይ የእድሜ ገደብ ላይ ከሚገኙት የእድገት መዳበር ደረጃ ፈጥኖም ሆነ ዘግይቶ የሚደርስበት ይሆናል። ስለተወሰኑ ወጣት ጎልማሶች የ እድገት መዳበር ሁኔታ አሳሳቢ ጉዳዬች ሲከሰቱ፣ ወላጆች ወይም ሌሎች ተንካባካቢዎች፣ ሀኪሞችን ወይም ሌሎች የእድገ ት መዳበር ባለሙያዎችን ማማከር አለባቸው።

አካላዊ መዳበር (Physical Development)

እድሜያቸው ከ 13 እስከ 17 ዓመት የሆኑ አብዛኛዎቹ የዐሥር ዓመታት ልጆች (teens)፤

- ከልጅነት ወደ ጎልማሳነት የሚያደርሰውን አካላዊ ሽግግር እና ውርዝውና (Puberty) አጠናቀው ያበቃሉ።
- በተለይም ሴቶች የጉልምስና ቁመታቸው ላይ የሚደርሱ ሲሆን፣ [በአንጻሩ፣ ወንዶች ከከፍተኛው ሃያ ዓመታት እድሜአቸው ላይ እስኪደርሱ ድረስ እያዳአጉና እየረዘሙ ይሄዳሉ።]

የግንዛቤ መዳበር (Cognitive Development)

እድሜያቸው ከ 13 እስከ 17 ዓመት የሆኑ አብዛኛዎቹ የዐሥር ዓመታቶች (teens)፤

- በአማራጭ ዕውቀቶች አማራጮች ላይ እና በሚያስከትሉም ወጤቶች ላይ በመንተራስ— የግንዝቤ ብስለት ደረጃ ላይ ይደርሳሉ።
- በአቻዎቻቸው ጫና ተጽእኖች ይመራሉ [ከለጋ የጉርምስና ወቅት በኋላ የአቻዎች ጫና እና ተጽእኖዎች ኃይል እያነሠ መጓዝ ይጀምራል።]
- በገዛ ራስ ለመቆም ክህሎቶችን ያዳብራሉ።
- ለብዙኃን መገናኛዎች ምላሽ በማድረግ፣ ከብዙኃኑ መገናኛዎች የሚመጡ መልእክቶችን ለመመርመር የሚያስችል እና እየጎ ለበተ የሚሄድ ክህሎቶችን ያዳብራሉ።
- ከጓደኞች እና ቤተሰብ ጋር እየጎለበት የሚሂድ የእርስ በእርስ ግንኙነቶችን ያዳብራሉ
- በሕይወታቸው ላይ ወሳኝነት የሚኖረው የጎለበተ ኃይል ይፈልጋሉ።
- ከጥገኛነት ለመላቀቅና ነፃነታቸውን ለመጨበጥ መኪና መንዳትን ይማራሉ።

የስሜት መዳበር (Emotional Development)

እድሜያቸው ከ 13 እስከ 17 ዓመታት ውስጥ ያሉ አብዛኛዎቹ በዐሥር ዓመታት እድሜ ውስጥ የሚገኙ ታዳጊ ወጣቶች፤

- እምነትና መተማመን፣ አዎንታዊነት ያለው የከዚህ ቀደም ልምድና ገጠመኞች እንዲሁም ስለ ፍቅር ግንዛቤ ምንነት ግንባታ መሠረቱ እስከ አላቸው ድረስ፣ ረጅምና ዘላቂነት ያለው፣ የጋራ የሆነ እና ጤናማ ግንኙነቶችን የማዳበር ችሎታዎች ይኖራ ቸዋል።
- የራሳቸውን ስሜቶች የመረዳት እና የዚህ ዐይነት ስሜትም ለምን ሊሰማቸው እንደቻለ የመተንተን ችሎታ።
- ለመልክ እና መስለው ስለሚታዩበት ገጽታ አነሥተኛ ግምት በመስጠት በአንጻሩ ለስእብና (personality) ከፍ ያለ ዋጋ ይሰጣሉ።

ጾታዊ ሁኔታዎች መዳበር (Sexual Development)

እድሜያቸ 13 እስከ 17 ዓመት ውስጥ ያሉ አብዛኛዎቹ በዐሥር ዓመታት እድሜ ያሚገኙ ታዳጊ ወጣቶች፤

- ቁንጅናዊ መስህብነት እንዳለባቸው ይህንንም የማንፀባረቁ ሁኔታ ሊያስከትል የሚችለውን ጣጣና ስለ አሉትም አማራጮች ይገነዘባሉ።
- ቁንጅናዊ መስህብነታቸውንም የሚገልጹባቸውን መንገዶች፣ የግብረ ሥጋ ግንኙነትን በማይጋብዝና በማያካትት ሁኔታዎች ምርጫዎች ያደርጋሉ።
- ጤናማና ጤናማ ያልሆኑ ግንኙነቶች የሚይዟቸውን ሁኔታዎች ለይተው ያውቃሉ።
- ስለ እርግዝና እንዲሁም ስለ ኤች አይቪ (HIV) ስለሌሎችም የአባላ ዘር ተላላፊ በሽታዎች ጉዳይ እንዲሁም የግብረ ሥጋ ግን ኙነት ሊያስከትል የሚችለውን ችግርና ጣጣ ምንነት በሚገባ ይረዳሉ፣ ግልጽ የሆነ ግንዛቤም ይይዛሉ። ከዚህም በተጨማሪ ስለ ግብረ ሥጋ ግንኙነት በተጨባጭ ዕውቀት ላይ በተመሠረተ ግንዛቤ ላይ በመንተራስ በጥብቅ የታሰበበትና ምክንያት አዘል ምርጫ ያደርጋሉ።
- ስለ ግብረ ሥጋ ግንኙነት አስተያየቶች ጉዳይ የብዙኅን መገናኛዎች የሚያራምዷቸው ነገሮችን ልብ በማለት ይገነዘባሉ።
- ስለ መወዳጀት፣ ፍቅር እና የረጅም ጊዜ ግንኙነት ሁኔታዎች የማወቅና የመማር ችሎታዎች አሏቸው።
- ስለ ገዛ እራሳቸው ቁንጅናዊ መስህብነታቸው ግንዛቤዎቻቸው እና ዝንባሌዎቻቸው [ይህ ከግብረ ሥጋ ፍላጎት ባህርይ የተለዩ ነው።] ግንዛቤዎች እሏቸው።

ቁንጅናዊ መስህብነት ያላቸውን ጤናማ ልጆች ለማሳደግ ወላጆች ማወቅ የሚገባቸው ጉዳዮች።

እድሜአቸው ከ 13 እስከ 17 ዓመት ሞላቸውን በዐሥራ የዕድሜ ክልሎች ውስጥ የሚገኙ ወጣቶችን ጤናማ የሆነ ቁንጅናዊ መስህብነትን ለማዳበር እንዲችሉ ለ መርዳት፣ ወላጆች ማድረግ ያለባቸው።

- ግብረ ሥጋ ግኑኝነትንና ንክኪነትን በሚመለከት በግልጽ የቤተሰብ እና የ ኃይማኖት እሴትዎን ይግለጹ። ምንም እንኳን የግብረ ሥጋ ግንኙነት አስደሳች ስሜት ቢኖረውም፣ ወጣት የሆኑ ሰዎች፣ የበሰሉ፣ የሚያፈቅሩ እና የሚወዱ እንዲሁም ኃላፊነት የመ ሸከም ደረጃ ላይ እስኪደርሱ ድረስ መታገስና እና መቆየት ይኖርባቸዋል።
- ሁላችንም በፍቅር የመዋደድና የመፈቃቀር፣ ፍቅርንም የምንገልጽባቸው በርካታ አማራጮች እንዳሉን ያስረዱ።
- እርስዎና በዐሥራዎቹ የእድሜ ክልል ውስጥ የሚገኙ ታዳጊ ልጅዎ ስለ ግብረ ሥጋ ግኑኙነትና ንክኪነት ጉዳይ የምታምኑበት ውሳኔ ላይ ለመድረስ፣ እድሜን፣ የጋራ ስምምነትን፣ በመከላከያ ዘዴዎችንና እርግዝና በማስወገጃ ሁኔታዎችን የመጠቀም፣ መፈቃቀርን፣ በመሳሰሉ ጉዳዬች ላይ በጋራ ተወያዩበት።
- ውሳኔዎቻቸውን መሠረት የሚያደርጉባቸውን ሁኔታዎች በማመቻቸት፣ በዐሥራዎቹ ዓመታት ክልል የሚገኝ የታዳጊ ልጅዎን ውሳኔ የማድረግ ችሎታውን ያጠናክራሉ።
- ስለ እርግዝና መከላከያ አማራጮች ጉዳይ በመወያየት፣ ስለ መከላከያ ኮንዶም አጠቃቀም ሁኔታ ተወያዩበት። መከላከያ ሳያደ ርግ የግብረ ሥጋ ግንኙነት ቢደረግ ስለ አስቸኳይ የእርግዝና መከላከያ እና STI ምርመራና ሕክምናን ጨምሮ ታዳጊ ልጅዎ
- ስላሉት አማራጮች ጭምር በማንሣት ተነጋገሩበት። በዚሁ ዐይነት እርግዝና ቢከተል፣ ማሳደግን እና ጉዲፈቻን (ለአሳዳጊ የመሰጠትን) አማራጮች ሊኖሩ በሚችሉት አማራጮች ላይ ተወያዩበት።
- ራስን ከሌላው አብልጦ ስለማየትና ሌሎችን መጠቀሚያ (exploitive behavior) ስለ ማድረግ ባህሪያት እና ለምንስ ጤናማ እንዳልሆነ እና (በአንዳንድ ሁኔታዎችም ዘንድ) በሕግ የሚያስጠይቅ ሕገ ወጥ ተግባር ስለመሆኑ ጉዳይ ተነጋገሩበት።
- ታዳጊ ወጣቶች በወደፊት መጪ ሕይወታቸው በርካታ እድሎች እንዳሏቸው እና አንዳንዶቹ አግብተው ትዳር ይዘው እንደሚ ኖሩ/እና ወይም ሌሎች ሌጣ/ወይም ልጅ አልባ ሆነው እንደሚቀሩ በማንሣት አጥብቆ እንዲረዳው እና እንዲያውቅ ያድርጉ ።
- በጣም ሁሉን አቀፍ በሆነ ቃላት በመጠቀም አንዳንድ ወጣቶች ጌይ፣ ሌዝቢያን፣ ባይ ሴክሸዋል ወይም ትራንስ ጀንደር (gay, lesbian, bisexual, or transgender) ሊሆኑ እንደሚችሉ ያስረዱ።

2000 M St NW, Ste 750 | Washington, DC 20036 USA | P: 202.419.3420 | F: 202.419.1448
www.advocatesforyouth.org